# ‘የትውልዶች አለመግባባት እስከ መቼ?’

**ፀጋዝአብ ለምለም ተስፋይ**

(ሽክም የበዛበት ትውልድ፡ 2009 እና

የምሥራቃዊት ኮከብ፡ 2010 መጻሕፍት አዘጋጅ)

የዓለም ታሪክ እንደሚያስረዳን የሰው ልጅ የትውልድ ቅብብሎሽ ኹለንተናዊ ትስስርና ግንኙነት/ቶች ውጤት/ቶች ነው፡፡ ትውልዶች በማይነጣጠልና ሊነጣጠል በማይችል መስተሳስሮች ውስጥ ኖረዋል፡፡ ይኖራሉም፡፡ እነዚህም ትውልዶች ከጊዜ አንጻር ያለፉ፣ ያሉና የሚመጡ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

ውስብስብ፣ ሰፊና ጥልቅ ከኾኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሀገራዊ ችግሮቻችን አስኳሎች መሐከል አንዱና ዋነኛው የትውልዶቻችን እርስ በራስ በመንፈስ ያለመዋሃድ አልፎ ተርፎ እርስ በራስ የምናደርጋቸው ኹሉን አይነት ትግሎች ናቸው፡፡

ይህንንም በሀገራችን አመራር ከአመራር፣ አመራር ከአባል፣ አባል ከአባል፣ ደጋፊ ከአባል፣ አመራር ከዜጎች፣ ዜጎች ከአመራሮች፣ አሰሪ ከሰራተኛ፣ መምህር ከተማሪ - - - ጋር በተለያየ አቅጣጫ ሊቀመጥ የሚችል - በገሃድ የሚታይ - በአደባባይ የሚስተዋል - ሊደበቅ የማይችል - በታሪክ የሚታወስ ግጭቶች፣ ፍትጊያዎችና ኹሉን የሚጠቀልሉ አለመግባባቶች መገለጫው ኾኖ ይታያል፡፡

ስለኾነም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊተላለፉ ከሚገባቸው ኹለንተናዊ ሀገራዊና ሕዝባዊ እምነቶች፣ እውቀቶችና ድርጊቶች አንጻር እጅግ የሰፋ አልተግባቦቶችን እንመለከታለን፡፡ ለዚህም በርካታ አብነታዊ ማሳያዎችን ማንሣት የሚቻል ቢኾንም በዋናነት ሁለት አበይት ማሳያዎችን እንመለከታለን፡፡

## 1.1 አብነታዊ ማሳያዎች

## አንደኛ፡ በፖለቲካ ኃይሎች

የሀገራችን የሥልጣን ፖለቲካ በገዥውም ኾነ በተፎካካሪዎች (በሀገር ውስጥ ኾነ ከሀገር ውጭ) ፓርቲዎች/ ድርጅቶች ከተማሪዎች እንቅስቃሴ አንሥቶ የነበሩ **በዋናነት** የሚያንቀሳቅሱት (አንቀሳቃሽ ከተንቀሳቃሾችና ከመሳሪያዎች ጋር በእጅጉ የተሳሰረና የተቆራኘ ሁለት ገጽታ ያለው እንደኾነ ሳይዘነጋ!) እንደኾነ የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡

ፖለቲካችን ዛሬም መሠረታዊ የሚባል የአስተሳሰብና አመለካከት ለውጥ ሳይኖረው ለረዥም ዘመናት እንደነበረው ሥልጣንን ዋነኛ መነሻውና መዳረሻው ብሎም ማዕከሉ በማድረግ እየተንቀሳቀሰና እየተናወጠ ይገኛል፡፡ ተገዥዎችም ኾነ ተመሪዎች በአንጻሩ

ከሀገራችን ከ106 ሚሊዮን በላይ ከሚኾነው የሕዝብ ብዛታችን በቁጥር እጅጉን የምንበዛው ከ70% በላይ የሚኾነውን የሀገራችን የሕብረተሰብ ክፍል የምንሸፍነው ትውልዶች የምንሽከረከረው በነዚሁ ጥቂት/ቶች አያቶቻችን ነው፡፡

አያቶቻችን ለመግዛትም ኾነ ለመምራት እርስ በራሳቸው ብቻ ሳይኾን በውስጣቸውም ሕብረትና አንድነት ስለሌላቸው ተቸግረዋል፡፡ እኛም እርስ በራሳችን እንዳንገዛዛና እንዳንመራራ የመግዣውና የመምሪያው ቦታዎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተይዘዋል፡፡ ለመያዝ ማስለቀቅ ቅድመ ኹኔታ ነው፡፡ ለማስለቀቅ ደግሞ እውቀት፣ ልምድ፣ ተሞክሮና ሲስተም የለንም፡፡ እንዳንፈጥር ደግሞ እነሱ ይዘውታል፡፡ እነሱም እኛን ይፈልጉናል፡፡ እነሱን አንፈልግም ብንል እንኳ የነሱ ፍላጎት/ቶች ሕልውና በኛ መኖር ላይ የተመሰረተ ነውና ይታገሉናል፡፡ የማይስማሙ እንኳ ቢኾኑ ለፍላጎት/ቶች ሕልውናቸው መሣሪያነት ይደራደሩብናል፡፡

ዛሬ በሀገራችን በገዥው ፓርቲና በወጣቱ፤ በተፎካካሪ ፓርቲዎችና በወጣቱ መሐከል ከፍተኛ ክፍተት አለ፡፡ ወጣቱ በኹለቱም ኃይሎች ደስተኛ አይደለም፡፡ እነሱም በወጣቱ ደስተኞች አይደሉም፡፡

አልፎ አልፎ ዋና ባይኾንም ዋና የሚመስል የአባት ልጅን የመምራት፣ ጎልማሶች ወጣቶችን የሚያንቀሳቅሱበትን ኹነት/ቶች ብንመለከትም የቴክኒክና የስትራቴጂ ልዩነት/ቶች ካልኾነ በቀር በአስተሳሰብና በአመለካከት ደረጃ የአያቶች ሚና ወሳኝ እንደኾነ አያጠያይቅም፡፡ ትግሎቹም በአይነት፣ በመጠን፣ በስርጭት፣ በስፋትና በጥራት የተለያዩ ቢኾንም በትውልዶቹ መሐከል እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡

## ኹለተኛ፡ በሃይማኖት ተቋማት መሪዎች

በጊዜ ሂደት ከሰው ልጆች ኹለንተናዊ ትግል/ሎች እና ለውጦች በመነሣት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የመጣ ቢኾንም በሀገራችን የረዥም ጊዜ ታሪክ ውስጥ የሃይማኖት ተቋማት ሚና እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡

እነዚህ ተቋማት በሕብረተሰብ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ/ዎች በተለይ በአኗኗር ዘይቤያቸው ላይ የነበራቸው ተጽዕኖ ከፍተኛ ከመኾኑም ባሻገር መሪዎቻቸው ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡

ዛሬ ግን የሀገራችን የሃይማኖት ተቋማት መሪዎች እርስ በራሳቸው የተከፋፈሉ፤ ስለአንድነት፣ ሕብረትና ፍቅር ዘወትር ቢደሰኩሩም እነሱ ራሳቸው አንድነት፣ ሕብረትና ፍቅር ስለሌላቸው ምዕመኖቻቸው እየሰሙ የማያደምጧቸው፤ ከምዕመኖቻቸው እጅጉን የራቁ ከፍ ሲል በምዕመኖቻቸው የተቀደሙ፤ ከልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ጋር የሚነታረኩ፤ እነሱ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸውን በሀሳብ ልዕልና መምራት የሚገባቸው ቢኾንም የልጅ ልጆቻቸውና ልጆቻቸው አያቶቻቸውን እንዲህ ማድረግ አለባችሁ ብለው የሚጠይቁበት፣ የሚያሳስቡበት፣ የሚያስፈራሩበትና የሚከራከሩበት፤ አስተማሪ፣ መሪ፣ መካሪና ገሳጭ መኾን ይገባቸው የነበሩ - ተማሪ፣ ተመሪ፣ ተመካሪና ተገሳጭ የኾኑበት፤ ስህተትን የማረም ሥልጣን የተሰጣቸው - ራሳቸው እንዲታረሙ የሚገፉበት፤ ሥርዓት፣ ወግ፣ ልማድ፣ ደንብና ሕግ አክብረው ማስከበር ይጠበቅባቸው የነበሩ - እንዲያከብሩና

እንዲያስከብሩ የሚጮህባቸው፤ ውሃ ከላይ ወደ ታች መውረዱ ተፈጥሯዊ ቢኾንም ውሃ ከታች ወደ ላይ መፍሰስን ግድ የሚልበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ለምን?

ምክንያቱም አያቶች እርስ በራሳቸው፤ አያቶች ከልጆችና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር *ምክንያቶቹ ምንም ይኹኑ ምን* በእምነት፣ በእውቀትና በድርጊት ደረጃ እንደግለሰብ፣ እንደቡድንና እንደተቋም **በመንፈስ መግባባት** ስላልቻሉ - ስላልቻልን፡፡

ይህም በመኾኑ የተነሣ በሀገራችን **እንደሀገር ፍቅር፣ ተስፋ፣ እምነትና ደስተኛነት በትውልዶች መሐከል እንዳይኅላ** ኾኗል፡፡ ዕውን በሀገራችን የመሪና የተመሪ ፍቅር አለ? በሀገራችን በመሪና በተመሪ መሐከል መተማመን አለ? በሀገራችን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ነባራዊ፣ ወቅታዊና የወደፊት ጉዞ ማን ነው ደስተኛ? ማን ነው ተስፈኛ? ማን ነው ደስተኛነትና ተስፈኛነትን ሊያበስር የሚችለው?

በሥልጣን ፖለቲካችን በገዥውም ኾነ በተፎካካሪ ኃይሎች፤ በሃይማኖት ተቋማት መሪዎችና ምዕመናን መሐከል ያለው መራራቅና መቃረን፤ የመራራቁና የመቃረኑን ማሳያ ባጭሩ እናስቀምጥ ቢባል *የትውልዶች አለመግባባት* - አያቶች ከልጆቻቸው ጋር የሚያደርጉት ትግል ነው፡፡ ልጆች በአያቶቻቸው ሥር ላለመኾን ይታገላሉ፡፡ አያቶች ከልጆቻቸው ዘለው ከልጅ ልጆቻቸው ጋር ሲነታረኩ ይውላሉ፡፡

በኢትዮጵያ የልጅ ልጆች አርዓያ አጥተው - በሀሳብ ልዕልና በመንፈስ አንድ አድርጎ የሚመራቸው፣ የሚኮሩበት፣ **መምህራችን - መሪያችን - አባታችን - አያታችን** የሚሉትን አጥተው ይንገላታሉ፡፡ ከኹሉ የሚከፋው ካለፉ ትውልዶች ኹሉ በቁጥር የሚበዛው ይህ አዲሱ ትውልድ ከዚህ መንገላታት ያተረፋቸው እርስ በራስ በመንፈስ፣ በእምነት፣ በእውቀትና በድርጊት እንደዜጋ በዜጋነታቸው ያለመግባባታቸው ጣጣ በአደባባይ የሚታይ ከመኾኑም በላይ የሚመጣው ትውልድ የሚታነጽበት መንገድ መሳሳትና አለመኖር ቀጣይ የዝችን ምስኪን አሳቢ አልባ ሀገር እጣ ፋንታ እጅግ የሚያሳስብ ያደርገዋል፡፡

መገለጫውም ዛሬ በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን የምናየው የልጅ ልጆች አያታቸውን ይሰድባሉ፣ ይዘልፋሉ፣ ያንጓጥጣሉ፣ ያዛሉ፣ ያስለቅሳሉ፡፡ በአንጻሩ አያቶች ከልጅ ልጆቻቸው በአስተሳሰብና አመለካከት፣ በእምነት፣ በእውቀትና በድርጊት መራራቃቸውን፤ መስማት እንኳ አለመደመጣቸውን፤ መታየት እንኳ አለመስተዋላቸውን፤ መከበባቸውን እንኳ እንደአርዓያ የማይታዩ መኾናቸውን ያስተዋሉ አይመስሉም፡፡ በሁለቱ መሐከል ያለው ስፋት እጅግ ሰፊ ነው፡፡

ለወላጆቹ የማይታዘዝ ልጅ እጅጉን ተበራክቷል፡፡ በልጆቹ ላይ ሥልጣን የሌለው ወላጅ እልፍ አላፍ ኾኗል፡፡ መከባበር፣ ትህትና፣ ፍርሃት፣ ፈሪሃ ፈጣሪ - - - ሰብዓዊ ዕሴቶቻችን ሳስተዋል፡፡ የዚህ ነጸብራቅ ከአኗኗራችን ባሻገር በተለይ እጅጉን ጎልቶ በማሕበራዊ ሚድያዎች ይታያል፡፡ ትላንትም ኾነ ዛሬ በሀገር ኹለንተናዊ መስዋዕትነት እያስከፈሉንና እየከፈልንባቸውም እንገኛለን፡፡

አያት በልጅ ልጆቹ እንዲያ መኾን ከማዘን፣ ከማንባት፣ ከመውቀስ፣ የትንቢቱ ፍጻሜ ነው ከማለት ባሻገር የነሱ የሥራ ውጤት፣ የነሱ ድርሻና የነሱ ተጠያቂነት እንዳለበት የጋራ መግባባት ላይ የደረሱና ቁጭት የፈጠረባቸው አይመስሉም፡፡ የልጅ ልጆች ከአባቶቻቸው

በመራቃቸው ስረ መሰራታቸው እንደተናጋና እንደሚናጋ ያስተዋሉ፡፡ ያስተዋልን አንመስልም፡፡

ትውልዶች እርስ በራሳቸው ያለፈው ካኹኑ፤ ያኹኑ ከሚመጣው ጋር ካልተከባበሩ፣ ካልተቀራረቡ፣ ካልተደማመጡ፣ ካልተማማሩ፣ ካልተራረሙ፣ ካልተቀባበሉ፣ ካልተናበቡና ካልተወራረሱ በቀር ደማቅ ታሪክ መስራትና ወደ ተሻለ ደረጃ የመድረስ ነገር ቅዠት እንደኾነ ገና የተገነዘብን አንመስልም፡፡ በኹላችንም ዘንድ ይህ ክፍተት እንደክፍተት እንቅልፍ ነሥቶ ሊያስነባን፣ ሊያስቆጨንና ሊያንገበግበን የሚገባ ቢኾንም አለመኾኑ ገና ከጥልቅ የአላዋቂና ያላስተዋይ እንቅልፋችን እንዳልነቃን ያሳያል፡፡

የማንኛውም ሀገር ስኬት በትውልዶች ትስስርና ኹለንተናዊ ግንኙነቶች ላይ የተመሰረተ የርቢ ውጤት ነው፡፡ እርስ በራስ የማይደማመጡ ትውልዶች ያሉባት ሀገር ወደ አዘቅጥ እንጂ ፈጽሞ ወደ ሰኬት አምርታ አታውቅም፡፡ ልታመራም አትችልም፡፡ የማይናበብና የማይግባባ ትውልድ የመናበብና የመግባባት ፍሬ ፈጽሞ ሊኖረው አይችልም፡፡ **ትውልዶች ሆይ! እንቁም! እናስተውል! እንጠይቅ! እንመርምር! እንንጓዝ!** አለበለዚያ እኛ ገደል እንሰራ አልያም ወደ ገደሉ ለመግባት እየተጣደፍን ይኾናል እንጂ ገደሉ እንደኾነ ዘወትር በቦታው እንደነበረ፣ እንዳለና እንደሚኖር ታሪክና አኗኗራችን ሕያው ምስክር ነው፡፡ ፈጣሪ ሀገራችን **ነጻ ፍቃድን** የኹሉ ነገር **ማዕከል** ወደ ሚያደርግ **የዕሳቤ ሂደት** ትገባ ዘንድ ይርዳን!

**ቸር እንሰንብት!**